ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*

*ህዳር 23 ቀን 2008 ዓ.ም. የተላለፈ*

# የአንድን ትውልድ ታሪክ መግደል ፤ ሀገርን እንደ መግደል ይቆጠራል ።

ሀገር ማለት፤ ሜዳው ሸንተረሩ፤ ጫካና ሸለቆው፤ ወንዙና ባህሩ ብቻ ሳይሆን ፤ በውስጡ የሚኖሩትን ሕዝቦችንም ያቀፈ መልከዐ ምድርም ጭምር ነው ። ሀገርን፤ ሀገር ብሎ ለመጥራት ከተፈለገ፤ በውስጡ የሚኖሩ ሰዎች እንዲኖሩ የግድ ይሆናል ። ያለ ሕዝቦች ሀገር የሚባል ነገር አይኖርም ። ሀገር የሚባለው ፤ በውስጡ ዜጎችን አቅፎ በመያዙ እንጅ፤ ዜጎች ከሌሉበትማ ምድረበዳ ከመባል በስተቀር፤ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም ። ይህ ሀቅ፤ ተፈጥሮና ታሪክ የሰጡት መሠረታዊ ትርጉም አለው ።

ሕዝብ የሌለበት መልከዐ- ምድር ሀገር ሊባል አይችልም ። በመሆኑም ፤ ምድረበዳ ተብሎ ከመጠራት አይዘልም ። ሰሓራ በረሃ ፤ ጎቢ በረሃና ካላሃሪ በረሃ ፤ ሁሉም ምድረ በዳዎች ናቸው ። ሰው ሰለማይኖርባቸው ፤ ሀገሮች ተበለው አይጠሩም ። ምድረበዳዎች፤በረሃዎች ( Deserts ) ተብለው ነው የሚጠሩት ። ሕዝብ ፤ የሀገር ማዕካላዊና ዓይነተኛ መሠረት ነው። ሕዝብ ሳይኖር፤ ሀገር አለ ቢባል፤ የቅኝ ግዛትን ለማስፋፋት ከሚደረግ የቅኝ ገዢዎች አስተሳሰብ የተለየ ሊሆን አይችልም ። ቅኝ ገዥዎች፤ ፍላጎታቸው የሚወሩትን ሀገር እንጅ ፤ ነዋሪው ሕዝብ ቢጠፋ ባይጠፋ ደንታ አይሰጣቸውም።

ኢትዮጵያን፤ በኢትዮጵያዊነቷ እንደ ሀገር ዘልቃ እንድትቀጥል ያደረጓት፤ ተፈራራቂ ትውልዶች ነበሩ። እነርሱም፤ ዐርበኞችና ጀግኖች፤ ሀገር -ወዳዶች እንጅ፤ ራስ ወዳዶች አልነበሩም ። የስድሳ ስድስቱ መሥዋዕታዊ-አብዮታዊ ትውልድም ፤ የህይወት መሥዋዕት እየከፈለ ያለፈው፤ የእነርሱን ፈለግ በመከተል ነበር ።

ይህ ዐርበኛና ሀገር ወዳድ ትውልድ፤ መሥዋዕት ስለከፈለ፤ ሊወቀስ፤ሊነቀስ አይገባውም ። አኩሪ ታሪኩም ፤ የሚመሰገንና የሚከበር እንጅ፤ የሚነቀፍና የሚዋረድ ሊሆን አይችልም ። ታሪክ የሌላቸውና ታሪክንም መስራት ያልቻሉ፤ ግን የትውልዱን ታሪክ "ሊያቆሽሹ" ይሞክራሉ።

ከቶውንምና በተለይም፤ በሦስቱም አምባገነን ገዥዎች ስር በአገለገሉ ግለሰቦች ሊነቀፍ አይችልም። ነቃፊዎቹ፤ የሞራል ሥልጣንም ይሁን፤ የሚያስከብር ስብዕና የላቸውምና ! **" ዕድሜ ዘልዝላ ነው "** እንደሚባለው ሆኖ ነው መሰል ፤ በዕርግና ዘማናቸው ፤ ተከብረው እንዳይኖሩ ራሳቸውን እየኮነኑ ይኖራሉ ። ኀልፈተ- ቀናቸውን በንሰሃ መጠበቅ ሲገባቸው፤ የዚያን ጀግና ትውልድ ታሪክ ጥላሸት ለመቀባት ይንከላወሳሉ ። ያ ትውልድ፤ ግን ያዝንላቸዋል እንጅ አያዝንባቸውም ! ከራሳቸው ጋር ታርቀው ከመጡም በፀጋ ይቀበላቸዋል ። ይህንንም የሚያደርገው፤ የሞራል ሥልጣን አለኝ ብሎ፤ በራሱ ስለሚተማመን ነው ።

ኢትዮጵያ ሀገራችንም ሀገር ነች የምንላት ፤ ሁላችንም ዜጎቿ ስለምንኖርባት እንጅ አፈሯንና አየሯን ብቻ በስሌት አስግብተን አይደለም ። ሕዝብ ነን ስንል ደግሞ፤ ኖረው ያለፉትን፤ አሁን የሚኖሩትንና ወደፊት የሚተኩትን ተከታታይ ትውልዶች አካትተን፤ ደምረንና አጠቃለን ስናስብ ነው። እኛ፤ የኢትዮጵያ ሀገራችን ዜጎች ናቸው የምንላቸው ፤ በሀገራችን ኖረው ያለፉትን አያት፤ ቅድመ-አያት ፤ አሁን ያሉትን ዜጎችንና የሚመጣውንም ተተኪ ትውልድ በግምት ውስጥ አስገብተን ነው። የኢትዮጵያ ዜጎች ናቸው ለማለት የሚቻለውም ፤ የሦስቱም ድምር ውጤት፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ስለሆኑም ነው ።

ይህ ሃቅ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤የሀገር ኀልውና፤ የፖለቲካና የህግ ትርጉም እንዲሰጠው ካስፈለገ፤ ሦሉስ (ሦስትዮች) መስፈርቶች እንዲኖረው ግድ ይሆናል። እነርሱም፤

1ኛ. የግዛት አንድነቱና ልዕልናው በህግ የታወቀለት ዳር-ድንበሩንም ያስከበረ/የተከበረ መሬት፤

2ኛ. በዚህ መልከዐ ምድራዊ ውስጥ የሰፈሩ ዜጎችና

3ኛ. ዜጎቹ ተስማምተው የመሰረቱት መንግሥት ናቸው።

በወቅቱ ባሉት ኢትዮጵያውያን ዜጎች አስተሳሰብ ፤ ዛሬ ሦስቱም የደበዘዙ እንደሆኑ ይቆጥሯቸዋል ። ምክንያቱም፡-

**ሀ.** የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና (Territorial Integrity ) ዳር ድንበር ያለተጠበቀና እንዲያውም፤ በየጊዜው እንደ ባኅር አሸዋ እየተሸረሸረ በመሄድ ላይ በመሆኑ ነው። የሀገሪቱ የቆዳ ስፋትም ፤ ጀርት እንደበላው ዱባ እየተሸራረፈ በመሄድ ላይ ይገኛል ።

**ለ.** ዜጎቿም፤ በጎሳና በነገድ ተከፋፍለው እንዲበታተኑ የሚያስገድድ ህግ በመውጣቱ ፤ ( አንቀፅ 39) ኢትዮጵያዊነታቸው የአንድ ሀገር ዜጎች እንዳይቆጠሩ ስለአደረጋቸው ነው ።

**ሐ.** ኢትዮጵያውያን ዜጎች ፈቅደውና ወስነው የመሰረቱት መንግሥት ባለመኖሩ ነው ።

ይህ ሁኔታና በደል አልበቃ ብሎ፤ እንዲያውም በከፋ መልኩ ዛሬ ያንን አሳረኛ ትውልድ፤ ያን ለሀገሩና ለወገኑ መሥዋዕት የከፈለን ትውልድ ታሪክ ለማጥፋት ከፍተኛ ዘመቻ እየተደረገ ይገኛል ።

የአንድን ሀገር አርበኛና ጀግና ትውልድ ፤ ታሪክ እንዲጠፋ የሚደረገው ጥረትና ሙከራ፤ የሀገሪቱን መላ ሕዝብ ታሪክና ኅልውና ከማጥፋት ተለይቶ የሚታይ ሊሆን አይችልም ። የሀገርን መጥፋት፤ ከአንድ ትውልድ ታሪክ መጥፋት ጋር የተየያዘ መሆኑን ሳይረዱ ፤ ያን ትውልድ ከመጥላት በመጣ ምክንያት ብቻ ፤ የታሪክ ግድያ ማካሄድ ማለት፤ የዚያን ትውልድ ዘር ከማጥፋት የተለየ ሊሆን ከቶ አይችልም ።

የአንድን ሀገር ትውልድ ታሪክ በተወሰነ የዕድሜ ክልል ብቻ ፈርጆ ፤ መክሰስና መኮነን ፍርደ-ገምድል ከመሆኑም በቀር ፤ ኢ-ምክንያታዊም ነው። መሃይምነት የጠነሰሰው የጅምላ አስተሳሰብና ኋላ ቀር የሆነ፤ ትውልድ -ገዳይ ወንጀልም ነው ። ይህንን ወንጀል በመፈፀም ላይ የሚገኙ ሰዎች፤ መካሪ ካላቸው ሊመከሩ ይገባል ። መከሪ ከሌላቸው ደግሞ፤ መከራ እንደሚመክራቸው መገንዘብ አለባቸው ። የተዳፈነ እሳት ፤ የጠፋ መስሏቸው ዐይነ- ኅሊናቸውን ጨርሰው መጥፋት አይገባቸውም ።

ያ ትውልድ፤ ሲበዛ ሀገር-ወዳድ ፤ ሕዝብ አፍቃሪ ፤ ለደሃ ተቆርቋሪ ፤ ነበር። ፍርድ ተጓደለ፤ ሕዝብ ተበደለ፤ ዜጋ ተራበ-ታረዘ፤ ብሎ በመነሳት፤ አይከፍሉ መሥዋዕት የከፈለ ቆራጥ ጀግና ትውልድ ነበር ። ለሚወዳት ሀገሩና ለሚያፈቅረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቤዛ በመሆን እንደ ጧዛ የረገፈ ትውልድ ነው ። መላ ህይወቱን ፤ ለመሥዋዕታዊ ትግል እንዲውል የወሰነበት መንሥዔም ፤ በሚከተሉት መሠረታዊ ምክንያቶች ነበር ።

**1ኛ.** የሀገሩ በሥልጣኔ ወደ ኋላ መቅረት ፤ የዜጎቿ በጭቆና አገዛዝ ስር መወደቃቸው፤

**2ኛ.** ሁሉ ሞልቶ-ተርፎ እያላት፤ ሕዝቦቿ በረሃብና ጠኔ፤ በበሽታና በድኀነት እየተቆራመዱ መኖራቸው፤

**3ኛ.** ማይምነትና ድንቁርና ስር መስደዳቸው፤ የድሃውና የገበሬ ልጆች የትምህርት ዕድል ስለአላገኙ፤

**4ኛ.** ከኢትዮጵያ እጅግ ወደ ኋላ ቀርተው የነበሩ ሌሎች ሀገሮች ፤ በሁሉ ረድፍ ሀገራችንን እየቀደሟት መሄዳቸው፤ ያመጣው ቁጭት ፤ ከብዙ በጥቂቱ ዋናዋና ምክንያቶች ነበሩ ።

እነዚህን የሀገራችን ችግሮች ለማስወገድ፤ በግድ፤የሥርዓት ለውጥ መምጣት ስለነበረበት፤ የለውጡ አካል በመሆን ለመሥዋዕት ራሱን አሳልፎ የሰጠ ቆርጥ ትውልድ ነበረ። ነውም።

**ዓላማዎቹም የሚከተሉት ነበሩ፡-----**

**ሀ.** ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመስረትና ፤ፍትኀ-ርትዕ የሰፈነባት ሀገር ለማየት፤ ብሎም፤ ብዝበዛንና ጭቆናን ማስወገድ፤

**ለ.** የዜጎቿ ዕኩልነት የሚከብርባትና ሁሉም ሃይማኖቶች ህጋዊ-ተገቢ ቦታቸውን መያዛቸውን ማረጋገጥ፤

**ሐ.** ኢትዮጵያ ሀገራችን፤ ከማነኛውም ፤ የውጭ ባዕዳን ተጽዕኖ ነፃ ሆና፤ የራሷን ሀገራዊ ሉዓላዊነቷን ጠብቃና አኩሪ ታሪኳንም አስከብራ ፤ ዘለዓለማዊት ኢትዮጵያ ሆና እንድትኖር ናቸው።

ለነእዚህ ቅዱስ ዓላማዎች ሲባል፤ የመጨረሻውን መሥዋዕት የከፈለው ትውልድ ትህትና ባልጎደለው መልኩ ይኮራል እንጅ አያፍርበትም ። ይህንን በማድረግ ደግሞ የማንንም እውቂያ-እውቅና አይፈልግም ። ማንንም ይቅርታ የሚጠይቅ አይሆንም። በትግሉ ሂደት ለተከሰቱት ስህተቶች ግን ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ከመጠየቅ ወደ ኋላ የሚል አይደለም። አሁንም ፤ እንደ ትላንቱ ፤ የሀገራችን ቀንደኛ ጠላት የሆኑቱን የሩቅና የቅርብ ኃይሎች ፤ በፅናት ከመታገልም ግንባሩን አያጥፍም። ለአንድነትና ለሀገር ወዳድ ኃይሎችም የሚከተሉትን መልዕክቶች፤ ማስተላለፉን ይቀጥለበታል ፡---

**1ኛ.** አኩሪ ታሪካችንን እያከበርን ማሰከበር የሁላችንም ሀገራዊ ተልዕኮ ብቻ ሳይሆን፤ ግዴታችንም ነው። በመሆንም ፤ የዚያ ዐርበኛና መሥዋዕታዊ ትውልድ አባላት የሆናችሁ ሁሉ ፤ በያላችሁበት አኩሪ ታሪካችሁን እያከበራችሁ አስከበሩ !

**2ኛ.** በዘርና በቋንቋ ሊከፋፍሉን ሞክረው ስለ አልተሳካላቸው፤ አሁን ደግሞ በትውልድ (Generation ) ሊያበጣብጡን መሞከራቸውን አውቀን ፤ ሁላችንም የአንድ እናት ኢትዮጵያ ልጆች በመሆናችን፤ ትውልድ አጥፊ የሆነውን የጋራ ጠላት ዘረኛ ሥርዓት ተባብረን ማስወገድ አለብን ።

**3ኛ.** የኢትዮጵያ ነፃነትና ኀልውና የገድልና የመሥዋዕት ታሪክ መሆኑን አውቀን ፤ በአኩሪው የገድል ታሪካችን የምንኩራበት እንጅ ፤ የማንሻማቀቅበት መሆኑን ጠላቶቻችን እያንገፈገፋቸውም ቢሆን ሊያውቁት ይገባል ።

**4ኛ.** የጋራ ታሪክን እያሰከበሩ ፤ የጋራ ሀገርን ከአጥፊ ጠላቶቿ ማዳን የሁላችንም የጋራ ተግባር ስለሆነ ያ ትውልድ አስቦበት በጋራ እንዲነሳ ጥሪው ለሁሉም ይተላለፋል !

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !**